<u>*AMHARIC*</u>

## <u>በአሁኑ ወቅት ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመመረቅ ተማሪዎች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች በየወቅቱ የሚቀርቡ ጥያቄዎች</u>

**(1) አንድ ተማሪ ዲፕሎማ ለማግኘት ጥረት በሚያደርግበት ወቅት- ማለት ዋስልን ካለፈ ወይም በሁሉም ትምህርት አይነት ወይም እሱን የሚተካ ሌላ የተፈቀደ አማራጭን አሟልተው ነገር ግን ሂሳብን ስላሟሉ ለመመረቅ ሂሳብን የሚወስዱ ከሆነ መውሰድ ያለባቸው የሂሳብ ትምህርት አይነት ምንድን ነው ?**

ቢያንስ ለዘጠነኛና ለአስራኛ የክፍል ደረጃ ከተመደው ትምህርት ጋር የሚዛመድ ትምህርቶችን መውሰድ አለባቸው። ይህም ኢንተግሬትድ አንድ እና ሁለት የተሰኙ የሂሳብ ትምህርቶች፤ አፕላይድ ሁለትና ሶስት የተሰኙ የሂሳብ ትምህርቶች እንዲሁም ፓዝወይስ የተሰኘ የሂሳብ ትምህርቶችን።

**(2) ተማሪው እነዚህን ክፍሎች ከአማካይ ነጥብ በላይ በማግኘት ማለፍ ይኖርበታልን ?**

አይኖርበትም። ከተማሪው የሚጠበቀው ትምህርቱን ማለፍ ብቻ ነው። የሚያመጣው ነጥብ ኤ ወይም ቢ (ወይም እንዲሁም ሲ) መሆን አይኖርበትም። ተማሪው በሂሳብ ክፍል “ዲ” ቢያመጣም እንዳለፈ ይቆጠራል። የትምህርት ቤት አማካሪዎች ግን ከተማሪው ጋር በመመካከር የተማሪውን ችሎታ ሊያዳብሩ የሚችሉ መውሰድ የሚገባውን ትምህርቶች በመምረጥ በኩል አብረው ይሰራሉ። ለምሳሌ ኢንተግሬትድ ሁለት በተሰኘ የሂሳብ ትምህርት “ዲ’ ነጥብ ያመጣ ተማሪ ቀጥሎ የሚወስደው ትምህርት ኢንተግሬትድ ሶስት የሂሳብ ትምህርት ከመሆኑ ይልቅ አፕላይድ ሁለት የተሰኘ ሂሳብ ቢወስድ ይመረጣል።

**(3) የእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚወስዱ የባይሊንጓል ተማሪዎች ለመመረቅ የዋስልን ፈተና መውሰድ ይኖርባቸዋልን ?**

የዋሽንግተን ስቴት ህግ ደንጋጊ ክፍል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የዋሽንግተን የቋንቋ ምልከት ፈተና(WLPT ) ያላለፉ ተማሪዎች ዋስል እንዳይፈተኑ ያረቀቀውን ህግ በዋሽንግተን ስቴት አስተዳዳሪ በመሻሩ ምክንያት በአሁኑ ወቅት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እንደሌሎቹ መደበኛ ተማሪዎች ለመመረቅ የዋስል ፈተና ወይም የተፈቀደ ሌላ አማራጭ ማለፍ አለባቸው።

**(4) ከሌላ ስቴት ተዘዋውረው የመጡ ተማሪዎችስ ጉዳይስ ሁኔታው እንዴት ነው ?**

ከሌላ ስቴት የማለፊያ ነጥብ ይዘው የመጡ ተማሪዎች(ማንኛውም ተማሪ ወደ ኋላ መቅረት የለበትም የሚለውን ህግ ለማሟላት የተዘጋጁ ፈተናዎችን ያለፉ ተማሪዎች የዋስልን ፈተና መውሰድ አይኖርባቸውም። ሰርቲፊኬት ኦፍ ኣካዳሚክ ኣቺቭመንት ወይም ሰርቲፊኬት ኦፍ ኢንዲቪዥዋል ኣችቬመንት ሳይሆን ዲፕሎማን ያገኛሉ።

**(5) ካልምኔቲንግ ፕሮጀክት የሚባለው ለመመረቅ ተማሪዎች የሚያሟሉት የምረቃ ፕሮጀክት በስቴቱ በኩል የተደነገገና መሟላት ያለበት ነው። ይህ ፕሮጀክት በትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ በኩል ሊነሳ (waive)ይችላል ወይ ?**

አይቻልም። ነገር ግን የተማሪዎችን ጉዳይ የሚመለከተው እንደ ስቱደንት ኢንተርቬንሽን ቲም(SIT) ወይም ኢንዲቪዥዋል ኢዱኬሽን ፕላን (IEP) የመማር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ፕሮጀክት ለማሻሻል ሃሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

**(6) ረኒንግ ስታርት የተሰኘ በኮሌጅ የሚሰጥ ፕሮግራም የሚወስዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን በሚመለከትስ ጉዳዩ እንዴት ነው ? ኢንግሊዝኛ 101 እና 102 የሚወስዱ ተማሪዎች ፕሮጀክቱን ሊተኩ ይችላሉ ወይ ?**

አይችሉም። ትምህርት ቤቶች የረኒንግ ስታርት የሚማሩ ተማሪዎች፤ ለእንግሊዝኛ 101 እና 102 ተብለው የተጠናቀቁ የስራ ውጤቶችን ለፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ እንደ አንድ ክፍል እንዲቆጠርላቸው ሊፈቅዱ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህን ክፍሎች በደፈናው መውሰድ ግን ፕሮጀክቱን የሚተካ አይደለም።ለምሳሌ በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚያቀርቡትን ፕሮጀክት መከላከልና በቦርድ(ፓነል) ፊት ቀርበው መልስ መስጠት የሚገባቸው ከሆነ ትምህርት ቤቱ ለረኒንግ ስታርት ተብሎ የቀረበን የጥናት ወረቀት ሊቀበሉት ይችላሉ። ነገር ግን ተማሪውች በቦርድ(ፓነል) ፊት ቀርቦ የሰራውን የጥናት ወረቀት መከላከልና መልስ መስጠት መቻል ይኖርበታል።